ክቡር ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል
የመኢአድ ፐሬዚዳንት

የተከበራችሁ የመኢአድ የስራ አስፈጻሚ አባላት

የተከበራችሁ የመኢአድ አባላት

ጤና ይስጥልን በቅድሚያ ካናዳ በሚገኘው የመኢአድ ድጋፍ ድርጅትና አባላት ስም የከበረ ሰላምታ  አቀርባለሁ።

መኢአድ ባለፉት 12 ወራት ከፍተኛ የሆነ የውስጥና የውጭ ችግር ፈተና ገጥሞት ሳለ በቆራጥ አቋም፣ በጽናት፣ በዘዴና በትእግስት ተቋቁማችሁ መኢአድን እስከዛሬዋ ቀን ድረስ ጠብቃችሁ ላቆያችሁት አመራርና አባላት ከፍተኛ የሆነ አድናቆታችንና ምስጋናችንን ላቀርብ እወዳለሁ።

መኢአድ የተነሳበትን ዋና ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ሕዝብን አደራጅቶና አስተባብሮ ታሪክ የሰራ፣ የሕዝብና ሀያልነትና ወሳኝነት ያስመሰከረ እውነተኛ ሕዝባዊ ድርጅት በመሆኑ መሰረቱ የጸና ነው። በዚህም በጣም እንኮራለን።

ሆኖም ግን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የተነሳው ሀይል በየጊዜው መልካቸውን በሚቀያይሩ የውስጥ ሀይሎችና  ሰርጎ ገቦች  በኩል አፍራሽ መልዕክተኞች በመላክ ከዋናውና ከተነሳበት ዓላማ ተዘናግቶ በውስጥ ችግርና ጉዳይ ላይ እንዲያተኩር በመደረጉ ትግሉን በእጅጉ ወደ ¡ ላ ጎትቶታል እንላለን።

መኢአድ ላይ የሚደረገው ርብርቦሽና የጥፋት ዘመቻ በአንድ በኩል ከገዢው ፓርቲና ከመንግስት አካሎች፣  በሌላ በኩል የተሳሳተና የተዛባ መረጃ የሚያቀርቡ የመገናኛ ብዙሃን፣ ከወዲህ በኩል ደግሞ በአገር ቤት ያሉ አንጃዎችና በታኞች በመኢአድ ድጋፍ ስም በውጭ ካሉ ደጋፊዎቻቸው ጋር፣  ከወዲያ በኩል ደግሞ የተቃዋሚ ድርጅት ነን ብለው በአገር ቤትና በውጭ አገር ከተኮለኮሉት  ድርጅቶች በኩል የሚደረግበትን  መጠነ ሰፊ አፍራሽ ዘመቻ ተቋቁሞ መቆየቱና መትረፉ ተዓምር ነው ያሰኛል።

ዛሬ የምታደርጉት ስብሰባ የመኢአድን ህልውና የሚፈታተን ጊዜ በመምጣቱ በጥንቃቄና በዘዴ፣ በሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ መኢአድን ለማቆየት የሚያስፈልገውን መስዋዕትነት  ሁሉ መክፈል የሚጠይቅ በመሆኑ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

ያፈለገው ነገር ቢሆን መኢአድ ትግሉን ለመቀጠል የተለያዩ ስልቶችንና መንገዶችን በመጠቀም መኢአድን ማትረፍና የተነሳበትን ዐላማ ከግቡ ማድረሱ የማይቀር ጉዳይ መሆኑን ሁሉም ሊያውቀው ይገባል።

መኢአድ ሁላችንንም ከዚህ አስከፊ ስርዓት ሊያላቅቀንና አገራችንን ሊያድን የሚችለው በነጻ አስተሳሰብና በራሱ የትግል መንገድ ሲታገል እንጂ በመንግስት አካላት ትእዛዝና በግዳጅ አይደለም።

ዛሬ ለመኢአድ የፈተና ጊዜ ነው። ፈተናውን ማለፍ ይኖርበታል። የመኢአድ አመራርና አባላት ተመካክራችሁና ተወያይታችሁ ወስናችሁ የምትሄዱበትን መንገድ በካናዳ የምንገኝ ደጋፊዎች ሙሉ በሙሉ የምንደግፈውና ጩኸታችሁን የምናሰማ፣ ትላንትም የመኢአድ፣ ዛሬም የመኢአድ፣ ነገም የመኢአድ ደጋፊዎች ሆነን መውደቅ መነሳቱን ከእናንተው ጋር እስከ ድል ድረስ አብረናችሁ በጽናት የምንጓዝ መሆኑን እናረጋግጥላች ¡ ለን።

በተፈጠረው የውስጥ ችግር የተነሳ በውጭ የሚገኘው ድጋፍ የተዳከመው አንሰራርቶ ህዝብ እውነቱን እያወቀ ድጋፉን በሰፊው እንዲቀጥል ለማድረግ በምንችለውና በተገኘው የመገናኛ ብዙሃን በኩል በማስረዳት መረጃ በመስጠት እንቀሳቀሳለን እንታገላለን።

የተከበራችሁ የመኢአድ አመራርና አባላት፣

እናንተ በአገር ቤት ከገዢው ፓርቲና ከመንግስት አካላት እንዲሁም ከውስጥ በታኞችና አንጃኞች ጋር ስትፋለሙ፤ እኛም በውጭ አገር መኢአድ ላይ ከሚረባረቡትና ደጋፊውን ከሚበትኑት ጋር እየተፋለምን ነው። ሁላችንም በአሸናፊነት እንወጣለን ብለን እናምናለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ህልውና የሆነውን መኢአድን ለማዳን ዘወትር ከጎናችሁ እንቆማለን። በርቱልን።

የኢትዮጵያ አምላክ ትግላችሁን ይባርክ!

መኢአድ በአመራሩና በአባላቱ ተጠናክሮ ትግሉን ይቀጥላል!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

የመኢአድ ድጋድ በካናዳ
ቶሮንቶ፣ካናዳ

ሕዳር 30 ቀን 2004